# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 98 መጋቢት 23 2002 ዓ.ም


**ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።**

**ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!**

## በወ/ት ብርቱካን ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ ሁላችንም እንቅልፍ ሊነሳን ይገባል

ከግንቦት7 የተሰጠ መግለጫ መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም

በአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ቀጭን ትእዛዝ በቃሊቲ እስር ቤት በግፍ ታስራ የምትገኘው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የጤንነት ሁኔታ አሳሳቢ በሆነ ደረጃ ላይ መገኘቱን ለመረዳት ችለናል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ ያደረጉላት ዶክተሮች ተጨማሪ ህክምና እንደሚያስፈልጋት ቢያሳስቡም፣ በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ትእዛዝ ህክምና የማግኘት ሰብአዊ መብቷን እንደትገፈፍ ተደርጓል።

አረመኔው መለስ ዜናዊ ስለ ወ/ት ብርቱካን የጤና ሁኔታ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ "ትንሽ ክብደት ከመጨመሯ በስተቀር በጣም ደህና ነች ቤተሰቦቿም ይጠይቋታል" ሲል ለመሳለቅ ሞክሯል። ብርቱካን ከአመት በላይ በቆየችበት እስር ቤት ከስድስት ወራት በላይ እጂግ ጠባብ በሆነች ክፍል ውስጥ በብቸኝነት እንድትታሰር ተደርጓል። እንዲሁም የ70 ዓመት ባልቴት ወላጂ እናቷና የ5 ዓመቷ ህጻን ልጇ በየሳምንቱ ለ30 ደቂቃ እንዲጎበኟት ከመደረጉዋ በስተቀር፣ ከሰው ተገልላ የስነ ልቦና ስቃይ እንዲደርስባት እየተደረገ ነው። ይህ ሁሉ ግፍ የሚፈጸምባት በአንድ ምክንያት ብቻ ነው- ለእውነት በመቆሟ። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## "የኦሮሞ ህዝብ ከፖለቲካ ውድድሩ" እንዲወጣ እየተደረገ ነው ሲሉ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ገለጹ

የኦሮሞ ፌዴራሊስት ፓርቲ ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ቡልቻ ደመቅሳ የወያኔው አገዛዝ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑትን ሁሉ እያሳደደ በመምታት ላይ መሆኑን ገልጸው፣ ለዚህም ምክንያቱ በቁጥር በርካታ መሆናችንና ብዙ የተፈጥሮ ሀብት ያለን በመሆኑ ነው ብለዋል። የኦሮሞ ፌደራሊስት ፓርቲ መድረክ የተባለውን ድርጅት ከመሰረቱት ፓርቲዎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜም በተለያዩ አካባቢዎች ለምርጫ በሚወዳደሩ አባሎቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ ድብደባና ስቃይ እየደረሰባቸው እንደሚገኝ ገልጸዋል።

አቶ ቡልቻ በመግለጫቸው በኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጸመ ያለውን ግፍና በደጋፊዎቻቸውንና በአባሎቻቸው ላይ የሚደርሰውን ስቃይ ለወዳጅ አገሮችና ለኢትዮጵያ ህዝብ ማሳወቃቸውን ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜናም ወያኔ ኦፍዴንንና በዶ/ር መራራ የሚራውን ኦብኮን ለማፈራረስና ተለጣፊ ድርጅት ለመመስረት በከፍተኛ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል። ከእነዚህ ፓርቲዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የወያኔ ባለስልጣናት ለተለያዩ ሰርጎገቦች ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በመመደብ፣ ድርጅቶችን ለማፈራረስ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በወያኔ ተጽእኖ ምክንያትም በኦፌዴን ስም በመጪው ምርቻ ለመወዳደር ተመዝግበው የነበሩ ሰዎች እራሳቸውን ከተወዳዳሪነት እያገለሉ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

## በርካታ ነጋዴዎች በቫት ስም ወይኒ እንዲወርዱ እየተደረገ መሆኑ ተገለጸ

በአዲስ አበባ ጉምሩክ ጽህፈት ቤት ውስጥ ታስረው የሚገኙትን በርካታ ነጋዴዎች አነጋገሮ ዘገባውን ያጠናቀረው ሪፖርተራችን እንደገለጸው፣ ነጋዴዎቹ በቫት ማጭበርበር ስም ታስረው የሚገኙት ድርጊቱን በመፈጸማቸው ሳይሆን ድርጅቶቻቸው ለወያኔ ኩባንያዎች ከፍተኛ ተወዳደሪ ሆነው በመቅረብና ስጋት በመፍጠራቸው ነው። እንደ ዘጋቢያችን ገለጻ የአያት ሪል ስቴት ባለቤትን ጨምሮ በርካታ የከተማው ነጋዴዎች በጉምሩክ ቅጥር ግቢ ውስጥ ታስረው እንደሚገኙ ለመመልከት መቻሉን ገልጿል። የአዲስ አበባ ነጋዴዎች በከፍተኛ ፍርሀት ውስጥ እንደሚገኙ አንዳንድ ስማቸው እንዳያይጠቀስ የፈለጉ ነጋዴዎችን አነጋገሮ የገለጸው ዘጋቢያችን፣ ቫት የወያኔ አባልነት ፎርም ለመሙላትና የህወሀት ኩባንያዎችን የሚቀናቀኑትን ለመምታጥ ጥሩ ሰበብ መሆኑን አስረድቷል። የወያኔ ካድሬዎች ነጋዴዎችን የኢህአዴግ አባላት ከሆናችሁ ማንኛውንም አይነት ችግር እንቀርፍላችሁዋለን አለበለዚያ ግን ችግሮች ይገጥሙዋችሁዋል እያሉ እንደሚያስፈራሩዋቸው ነጋዴዎችን ጠቅሶ ዘግቧል።

## የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተባብሶ መቀጠሉን አምባሳደር ካርሰን አስታወቁ

በአሜሪካ የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ፀሀፊ የሆኑት አምባሳደር ካርሰን የአሜሪካ መንግስት በአፍሪካ ላይ የሚከተለውን ፖሊሲ ለመመርመር በተጠራ ጉባኤ ላይ እንደተናገሩት ፣ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ መሄዱን ገልጸው፣ አገዛዙ ይህን ሁኔታ እንዲያስተካክል ተደጋጋሚ ሙከራ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

የአፍሪካን ሁኔታ በዳሰሰው ጽሁፋቸው "አንዳንድ ምሁራንና የፖለቲካ ተንታኞች የአፍሪካ ዲሞክራሲ ከተራራው አናት ላይ ደርሶ ወደታች ተመልሶ እየወረደ መሆኑንና በምሳሌነትም በአፍሪካ ውስጥ የተጭበረበሩና ችግር የነበረባቸውን የኬንያ፣ የኢትዮጵያና የዝንባብዌን ምርጫዎች እንደሚያነሱ" አምባሳደሩ ገልጸው፣ አሜሪካ ለረጅም ጊዜ ወዳጅነት የምትመሰርተው ከአገሮች ጋር እንጅ ከመሪዎች ጋር አለመሆኑን የአፍሪካ መሪዎች ሊያውቁት ይገባል ሲሉ አስጠንቅቀዋል። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ስብስብ የመለስ ዜናዊን ንግግር አውገዙ

የትግራይ ተወላጆቹ "የህዝቡን ጆሮ በማፈን እውነትን መሸፈን አይቻልም" በሚል ርዕስ ያወጡት የአቋም መግለጫ፣ ከምርጫ በኋላ አንዳንድ ተቃዋሚዎችን ወደ ፍርድ እናቀርባለን በማለት አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የሰጠውን ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲሁም የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮን ከሩዋንዳ እልቂት ጋር በማመሳሰል ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርገውን ስርጭት እንደሚያፍን በይፋ መናገሩን የሚያወግዝ ነው።

የትግራይ ተወላጆቹ በዚሁ መግለጫቸው በቅርቡ ይካሄዳል ተብሎ የሚጠበቀው የይስሙላ ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሓዊና ሚዛናዊ እንዳይሆን የወያኔው አምባገነን አገዛዝ በምርጫው ለመሳተፍ እየተንቀሳቀሱ ባሉት ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ላይ የሚፈፅመው ግድያ፣ አፈና፣ ወከባና ጫና እየተባባሰ መሄዱን አውስቶ የወያኔው አገዛዝ ራሱ በሚፈጥረው ቀውስ ተዘፍቆ ወደ ተራ የአሸባሪነት ስራ በመሸጋገር በዜጎች ላይ ዓይን ያወጣና ጭካኔ የተሞላበት እርምጃዎች በመውሰድ ላይ እንደሚገኝ ገልጿል። በመቀጠልም የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ባለስልጣናት የረገጡት መሬት እየተናደባቸው መሆኑን **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## የወያኔው አምባገነን አገዛዝ ብርቱካን ሚዴቅሳን ለመጎብኘት በሄዱ ባልደረቦቿ ላይ አምባጓሮ አስነሳ

የቪኦኤው ዘጋቢ ፒተር ሃይንላይን ከአዲስ አበባ በላከው ሪፖርት ላይ እንደገለጸው ብርቱካን ሚዴቅሳን ለመጎብኘት ቃሊቲ ድረስ ሄደው የነበሩ ባልደረቦቿንና ጓደኞቿን መጎብኘት አትቺሉም በማለት መከልከሉን ዘግቧል። ፒተር በዚሁ ዘገባው ባለፈው ቅዳሜ እለት የወያኔው አምባገነን አገዛዝ ትእዛዝ ፈጻሚ በሆነው አበበ ዘሚካኤልና የመድረክ ፓርቲ ከፍተኛ የአመራር አካላትን ጨምሮ በሌሎች ጎብኚዎች መካከል ቃሊቲ እስር ቤት መግቢያ በር ላይ መፋጠጥ መፈጠሩን ገልጾ፣ በር ላይ በነበረው ፍጥጫ የሃገሪቱን የእስር ቤት ህግና ደንብ በሚያውቁት በነአቶ ስየ አብርሃ አማካኝነት የቀረበውን የመከራከሪያ ሃሳብ ባግባቡ አለመመለሱን ነገር ግን ብርቱካንን መጎብኘት የሚችሉ ከርሷ ጋር ዝምድና ያላቸው ግለሰቦች ናቸው በሚል መግባት እንደማይችሉ ገልጿል ብሏል። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## ገንዘብ ወደ ውጭ አገር የሚያሸሹ ያገዛዙ ባለስልጣናትና ባለሀብቶች መበራከታቸው ተሰማ

በግንቦት97 ምርጫ ማግሰት በርካታ የወያኔ ባለስልጣናት በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ወደ ውጭ አገር ማሸሻቸው በተለያዩ አለማቀፍ ሚዲያዎች ከተዘገበ በሁዋላ ፣ በዚህ አመትም ተመሳሳይ ድርጊት እየተፈጸመና ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ከውስጥ ወደ ውጭ በመሸሽ ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል። ገንዘባቸውን በማሸሽ ላይ ከተሰማሩት ማካከል ቅድሚያውን የሚይዙት የወያኔ ባለስልጣናት መሆናቸውን የአዲስ አበባው ሪፖርተራችን ከባንኮች የተገኘውን መረጃ ዋቢ በማድረግ የዘገበ ሲሆን፣ በከፍተኛ የስልጣን ደረጃ ላይ የሚገኙት ሰዎች ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ በአገር ውስጥ ካሉ ባንኮች ማውጣታቸውን ጠቅሷል።

ከወያኔ ባለስልጣናት በተጨማሪ የተለያዩ ባለሀብቶችም ገንዘባቸውን በአገር ውስጥ ከሚገኙ ባንኮች በማውጣት ላይ መገኘታቸውን ሪፖርተራችን አክሎ ዘግቧል።

ባለሀብቶቹና ባለስልጣናቱ በዚህ ሰአት ለምን ገንዘባቸውን ለማውጣት እንደፈለጉ ግልጽ የሆነ ምክንያት ባይኖርም ምናልባት መጪውን **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## ፍትህ በሰቆቃ ፈፃሚዎች ላይ ቁጣዋን ታወርዳለች!!!

የአንድነት ለዲሞክራሲና ፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር የሆነችው የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ አካላዊና ስነልቦናዊ ጤንነትን በተመለከተ ከቃሊቲ የሚደርሱን ዘገባዎች በእጅጉ የሚያሳስቡ ናቸው።

ከአንድ መቶ ሰማንያ ቀናት በላይ በጨለማ ቤት አስሮ፤ ከሶስት መቶ ቀናት ላላነሰ ጊዜ ደግሞ ከአስር ሜትር ስኩየር ባልበለጠ ጉሮኖ ውስጥ ገድቦ ተከታታይና ስልታዊ ሰቆቃዎችን ሲያስፈጽምባት የቆየው መለስ ዜናዊ “በእንቅስቃሴ ማነስ ምክንያት ክብደቷ ትንሽ ከመጨመሩ በስተቀር ብርቱካን በጥሩ ጤንነት ላይ ትገኛለች” ማለቱ የአረመኔነቱ መጠን ገላጭ ነው። መለስ ይህን ካለ ጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ ሺመልስ ከማል የተሰኘው ጥሩምባው የብርቱካን የጤንነት ጉዳይ ለምን አሳሳቢ ጉዳይ ተደርጎ እንደተወሰደ እንዳስገረመው ገልጿል። ብርቱካን እሱን እንዳይደለች አለመረዳቱ ደግሞ እኛን ገርሞናል።

ብርቱካን በወያኔ እስር ቤት ውስጥ ሰቆቃ እየተፈጸመባቸው ላሉት በብዙ ሺህዎች ለሚገመቱ ወገኖቻችን ተምሳሌት ናት። ህመሟ ህመማችን፤ ስቃይዋ ስቃያችን ነው። በእርሷ ላይ እየደረሰ ያለው በሺህዎች በሚቆጠሩ ወገኖቻቸን ላይ እየደረሰ ያለውን ስልታዊ ሰቆቃ አመላካች ነው። ወያኔ ያፈራቸው ድውያን በውስጣቸው ባለው የትንሽነት ስሜት ምክንያት በአስተሳሰብም ሆነ በሙያ የሚበልጣቸውን ሰው ማዋረድና ማሰቃየት ያስደስታቸዋል። በዚህም ምክንያት በመዳፋቸው ውስጥ በገቡ የፓለቲካ እስረኞች እንደ አስጊነታቸውና ታዋቂነታቸው መጠን የተለያየ ዓይነት ሰቆቃ ይፈጽሙባቸዋል። በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ እየደረሰ ያለው በደል ዓለም ዓቀፍ የዜና አገልግሎቶችም ዘግበውታል። እንዲህ አይነት የዜና ትኩረት ያላገኙ ሰቆቃዎች ደግሞ በርካታ ናቸው። መንግሥቴን ሊገለብጡብኝ ነበር ብሎ ባሰራቸው በእነ ጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ ብልት ቅጥቀጣ እና በኤሌክትሪክ ካውያ ጭንቅላት ማጋልን የጨመሩ ዘግናኝ ሰቆቃዎች ተፈጽመውባቸዋል።

ወያኔ ሰውን በማሰቃየት የሚደሰቱ እኩይ ፍጡራን ስብስብ መሆኑ አሁን ከኢትዮጵያዊያን አልፎ በመላው ዓለም የታወቀ ጉዳይ ሆኗል። በረሃ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ከእነሱ የተለየ አስተያየት የያዙ፣ አሊያም ወደፊት ይቃወሙን ይሆናል ብሎ የጠረጠሯቸውን ወዳጆቻቸውን ሳይቀር አሰቃይተዋል፤ ገድለዋልም። ነፃ ልናወጣው ተነስተናል ያሉት ሕዝብ በረሃብ ሲረግፍ ለምግብ መግዣ በተመፀወተ ገንዘብ ተምነሽንሸዋል። ከበረሃ ወጥተው መላው የኢትዮጵያን ከተሞችና ገጠሮችን በማጭበርበርም በጉልበትም ከተቆጣጠሩ በኋላም መሰሪ ሥራዎቻቸውን የሚቃወሙ ሰዎችን ማሳደድ፣ ማዋከብ እና ማሰቃየት የዘወትር ተግባራቸው ሆኗል። በርካታ ዜጎች የወያኔ ሰው በላ አውሬዎች ሰለባ ሆነው ሕይወታቸውን አጥተዋል፤ ከዚያ በቁጥር የበዙት ደግሞ ለዘላቂ የአካልና የስነልቦና ጉዳት ተዳርገዋል።

ሰቆቃ መፈፀም በሰብዓዊነት ላይ የሚፈፀም ዓለም ዓቀፍ ወንጀል መሆኑ ቢደነገግም በኢትዮጵያ እስር ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ እየሆነ ያለውን ዘግናኝ ሂትለራዊ ሰቆቃን ዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ እያወቀ በዝምታ ማለፉን መርጧል። የአሜሪካና የብሪታኒያ መንግሥታት ወያኔ ስለሚፈጽማቸው ሰቆቃዎች ያውቃሉ፤ በሪፖርቶቻቸውም በድርጊቶቹ ማዘናቸውን ይገልፃሉ። ይሁን እንጂ በእርዳታ ስም ሰቆቃውን ማስቀጠያ ገንዘብ ለወያኔ በመስጠት ስቃያችንን እያራዘሙት ነው። የእነዚህ አገራት መንግሥታት ተግባር በኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን በሰብዓዊነት ላይ የሚፈፀም ወንጀል ነው ብለን እናምናለን። አሜሪካና እንግሊዝ ወይም ሌሎች አገሮች የእኛን ትግል እንዲታገሉልን አንጠብቅም። ነገር ግን ከፋሺስታዊ ሥርዓት ጋር ወግነው የመከራ ጊዜዓችንን እንዳያረዝሙብን እንዲጠነቀቁ አበክረን እናሳስባለን።

ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ በዜጎቻችን ላይ የሚያደርሰው ሰቆቃ መቀጠሉ አይቀርም። በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ በእነ ጄኔራል ተፈራ ማሞ እና በሌሎችም ወገኖቻቸን ሁሉ ላይ እየተፈፀመ ያለው ሰቆቃ እንዲያበቃ ወያኔ ከሥልጣን መወገድ ይኖርበታል። ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከዲሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ኃይሎች ጋር በማበር ወያኔን ከሥልጣን አስወግዶ በምትኩ ለሰብዓዊ መብቶች ክብር ያለው ፍትሃዊ ሥርዓት ለመመሥረት ቆርጦ ተነስቷል፤ ለዚህም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ እንዲነሳ ጥሪ ያደርጋል።

በወገኖቻቸን ላይ ሰቆቃ መፈፀም ይቅር የማንለው ወንጀል ነው። ነገ ተጠያቂነትን ማስከተሉ ፈጽሞ አይቀርም። ያኔ “ታዝዤ ነው የፈፀምኩት” ማለት ተቀባይነት አይኖረውም። ወገኖቻቸን ላይ እየደረሰ ባለው ሰቆቃ እጃችሁን ያስገባችሁ ሁሉ ተገቢውን ቅጣት የምታገኙበት ቀን ቅርብ መሆኑን እየነገርናችሁ ነው። ሽራፊ እንኳን ህሊና ያላችሁ ካላችሁ ዛሬውኑ እጃችሁን አውጡ፤ ሰቆቃን አጋልጡ፣ ታገሉ። አለበለዚያ ግን እናንተ የማታውቋት፤ አድልዖን የማታውቀው ፍትህ ቁጣዋን ታወርድባችኋለች።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## በወ/ት ብርቱካን ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ወ/ት ብርቱካን በአምባገነኖች ትእዛዝ ወህኒ እንድትወርድ ከተደረገችበት ጊዜ ጀምሮ፣ የግንቦት7 ንቅናቄ የወያኔን አገዛዝ ድርጊት በማውገዝ ተደጋጋሚ መግለጫ ሲያወጣ ቆይቷል፤ ብርቱካን ምንም አይነት ወንጀል ሳትሰራ በአምባገነኖች ትእዛዝ የታሰረች የህሊና እስረኛ መሆኑዋን፣ ወንጀል አለባት ከተባለም ወንጀሉዋ ለእውነት መቆሟ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገልጽና የወያኔን እርምጃም ሲያወግዝ ቆይቷል።

እስካሁን ስናደርገው ከነበረው ሁኔታ በተለየ ይህን አስቸኳይ መግለጫ እንድናወጣ ያስገደደንም የጀግናዋ የነጻነት ታጋይ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የጤንነት ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን በመረዳታችን ነው። በመሆኑም ግንቦት7 ወ/ት ብርቱካን በግፍ ከታሰረችበት እስር ቤት በአስቸኳይ ተለቃ፣ በተሻለ አገር ሙሉ ህክምና የምታገኝበት መንገድ እንዲፈለግ ጥሪ ያቀርባል። የብርቱካን ጉዳይ ማንኛውንም ነጻነት ወዳድ የሆነ/ች ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንቅልፍ ሊነሳው/ት ይገባል እንላለን። ለነጻነት የምንታገል፣ ስለነጻነት የምንዘምር ሀይሎች ሁሉ ወ/ት ብርቱካን በአስቸኳይ ከእስር እንድትፈታ፣ የጀመረችውን ትግል በሙሉ ጤንነት እንድትቀጥል ከዛሬ ጀምሮ ጠንካራ ትግል ማድረግ ይጠበቅብናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## የወያኔው አምባገነን አገዛዝ ብርቱካን ሚዴቅሳን . . . ከገጽ 1 የዞረ

የወያኔው አምባገነን አገዛዝ ምንም እንኳን በእለቱ በተፈጠረው ውዝግብ የቃሊቲ ወህኒ ቤት ሃላፊ ተብየው ብርቱካንን መጎብኘት የሚችሉ ከርሷ ጋር የስጋ ዝምድና ያላቸው ብቻ ናቸው ቢልም፣ ከበርካታ ወራቶች ጀምሮ ቀደም ብላ ብርቱካንን ትጎበኝ የነበረቺ እህቷ እንዳትገባ የተከለከለች መሆኑ እንደሚታወቅና ከ76 ዓመት ባልቴት እናቷና ከ5 ዓመት ህጻን ልጇ በሳምንት የ30 ደቂቃ ጊዜ ጉብኝት ውጪ ማንም ሰው እንዲጎበኛት አለመፈቀዱ የዚህ ጨካኝ መንግስት ዋና መገለጫዎች እንደሆኑ ግንቦት 7 መዘገቡ ይታወሳል።

## የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተባብሶ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በሚቀጥሉት ሁለት አመታት በአፍሪካ 27 ምርጫዎች እንደሚደረጉ ያወሱት አምባሳደር ካርሰን ፣ የአሜሪካ መንግስት ምርጫዎቹ በነጻና ፍትሀዊ መንገድ እንዲከናወኑ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

የውይይቱ መሪ የነበሩት ኮንግረስ ማን ዶናልድ ፔይን የኢትዮጵያን የተበላሸ ሰብአዊ መብት አያያዝ በተመለከተ ለአምባሳደሩ ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን፣ አምባሳደር ካርሰንም “በሚመጣው ምርጫ ላይ ትልክ ትኩረት ሰጥተን እየሰራን ነው። መንግስትና ተቃዋሚዎች ሀላፊነት በተሞላበት መንገድ እንደሰሩ ነግረናቸዋል። እንደ ግንቦት97 አይነት የተበላሸ ምርጫ እንዲደገም፣ በአዲስ አበባ ድጋሜ ግድያ እንዲደረግ አንፈቅድም። መንግስት ምርጫውን ነጻና ፍትሀዊ እንዲያደርግ ነግረነዋል። የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ሁኔታ እያሽቆለቆለ ነው። የአሜሪካ መንገሰት የስቴት ዲፓርትመንት በደንብ አድርጎ ነገሩን እየመዘገበ ነው። መንገሰት ሁሉንም ሰዎች በእኩል አይን እንዲያይ ነግረነዋል።

ወ/ት ብርቱካንን ጨምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ በእስር ላይ ስለሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች ለተጠየቁት ጥያቄ ደግሞ አምባሳደሩ “ብርቱካንን በተመለከተ ለኢትዮጵያ መንግስት ተደጋጋሚ ጥያቄ አቅርበናል። በቅርቡ ትፈታለች ብለን እየጠበቅን ነው። ከመለስ ጋር ባደረግነው ውይይት አብዛኛውን ጊዜ የጨረስነው በዲሞክራሲ ጉዳዮች ላይ በመወያየት ነው። ብርቱካንን የመሰሉ ሰዎች መታሰራቸው የኢትዮጵያን መንግስት ምስል እያበላሹ መሆኑን ሳይቀር ነግረናቸዋል። በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ መካከል ያለው ግንኙነት ሊቀጥል የሚችለው የኢትዮጵያ መንግስት የሰብአዊ መብት አያያዙን ሲያስተካካል ብቻ መሆኑን ተናግረናል።” የሚል መልስ ሰጥተዋል።

የመለስ አገዛዝ የአሜሪካን ድምጽ ለማፈን የወሰደውን እርምጃ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ደግሞ “ በአለም ላይ የእኛን ሬዲዮ እናፍናለን ብለው በይፋ ከተናገሩ ሁለት ወይም ሶስት አገሮች አሉ። አንዱ ሰሜን ኮሪያ ነው ሌላው ደግሞ ኢራን ነው። እኔን በጣም ያሳሰበኝ ነገር የአሜሪካን ራዲዮ ከሩዋንዳው ሚል ኮሊን ራዲዮ ጋር ማመሳሰላቸው ነው። ይህ አይነት ንጽጽር መደረግ ያልነበረበት ነው። ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው ነገር ነው። ተቃውሞዋችንን በግልጽ አስቀምጠናል።” ብለዋል።

## ገንዘብ ወደ ውጭ አገር የሚያሸሹ ያገዛዙ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ምርጫ ተከትሎ ሊፈጠሩ ከሚችሉ ሁኔታዎች ጋር ሊያያዝ እንደሚችል ሪፖርተራችን አስተያየቱን አስፍሯል።

ከአንዳንድ የውጭ መንግስታት ሰራተኞች በተገኘው መረጃ መሰረት ደግሞ የበርካታ አገሮች ኢምባሲዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የውጭ አገር ባለሀብቶች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ማሳሰቢያ በመስጠት ላይ ናቸው። መረጃው እንደሚያሳየው ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች ገንዘባቸውን በማሸሽ ላይ መገኘታቸው የየአገሮቹ ኢምባሲዎች ተጨማሪ ስጋት እንዲፈጠርባቸው ያደረገ ሲሆን፣ የኢምባሲ ሰራተኞችም ለባለሀብቶቹ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በመምከር ላይ ናቸው።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 98 መጋቢት 13 2002 ዓ.ም፤ ገጽ.3

## ውጭ ጉዳይ ሲገለጥ
## *የሰዩም ነገር*

**ክፍል 4 ካለፈው የቀጠለ**

### የላይብረሪዉ ስብሰባ

በመ/ቤቱ ላይብረሪ ወስጥ ለሰራተኞች ት/ት ይሰጣል።ሰራተኛዉ በሙሉ ሰራ ዘግቶ ሁለት ሳምንት ሙሉ አደንቁዋሪ ት/ት ሲማር ከረመ።ካስተማሪዎቹ መካከል አነዱ ያቅም ግንባታዉ ሚንሰቴር ተፈራ ዋልዋ ነበር።መሬትን በተመለከተ "መሬት አይሸጥም አይለወጥም" "over our dead body" እያለ ማስተማር ሲጀምር አጠገቤ ቀጭ ብሎ የነበረዉ አንድ የከተማ ልጅ ትን ብሎት ሳሉን ማቆም ስላልቻለ ሰበብ ሆነዉና እንደ ወጣ ቀረ።እኔም ትን እነዲለኝ እየተመኘዉ ከዚያ ሙት ክፍል ውስጥ ዉየ በፖለቲካ ዉስጥ "over our dead body" ማለት ካልሞትኩ በቀር ስልጣንኔን አለቅም ማለት መሆኑን ተምሬ ዉልቅ አልኩ። ከተፈራ በፊትና በሁዋላ ብዙ ህወሀቶች መጥተዉ ሲያደነቁሩን ሰነበቱ።የማልረሳዉን አንዱን እዚህ ጋ ማንሳት ወደድሁ። ከታወቁት ምሁራን መካከል አንዱ የሆነዉን ዶ/ር ክንፈ አብርሃን።

ዶ/ር ክንፈ አሁንም ሌላዉ ትግሬ ነዉ። እርሱም ይበለፅግበት ዘነድ የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሰላምና የልማት ተቋም ተሰጠቶታል።ከእርሱ ዲስኩር በሁዋላ የተናደዱ የትግራይ ልጆች በድፍረት ተናገሩት።'ተቋሙ የአንድ ሰዉ ብቻ ሆነ ስሙም የዶ/ር ክንፈ ተቐም ነዉ የሚባለዉ የሚሰጠዉም ስልጠና እኛን የሚመጥን አይደለም' ምና ምን እያሉ ዉርጅብኝ አወረዱበት።ዶ/ሩም "እያንዳንድሽ እንዴት እዚህ መ/ቤት እንደተቀጠርሽ እናዉቃለን በችሎታ ቢሆን ኑሮ ቦታሽ እዚህ አልነበረም" ብሎ አምርሮ ተናገር።ከዚህ በሁዋላ ራሱ ስዩም መጥቶ የከስረ ስብሰባ ብሎ አዝኖ ተናገረ። እኛም የስዩምን ሀዘን ሰምተን ዝም አልን።

ዶ/ር ክንፈ ከታወቁት ይሉኝታ ቢስ የህውሃት ሰዎች መካከል አንዱ ነበር። ይህ ሰዉ የኢትዮጵያንና የስዊዲንን ፓስፖርት ይዞ እደ ልቡ የሚኖር ነዉ። አንድ ቀን እንዲህ ሆነ፤ ይህ ዶ/ር ከዉጭ አገር ከህግ ውጭ እቃ ያሰገባና ቀረጥ መክፈል እምቢ ይላል። ምነዉ ቢባል እኔ የዉጭ አገር ሰዉ ነኝ የምስራዉም የአማካሪነት ሰራ ሰለሆነ የዲፕሎማቲክ መብት አለኝ በመሆኑም እቃዉ ይግባልኝ ብሎ ሙግት ይዛል። እንዲህ ከሆነ ደብዳቤ አምጣ ይባልና ጉዳዩ ወደ ውጭ ጉዳይ ይመጣል።ይህን ጉዳይ የሚከታተል አንድ ሰራተኛ ይህ ሰዉ እንዴት የሁለት አገር ዜጋ ሊሆን ይችላል ብሎ የነገሩን ሕገ ወጥነት ገልፆ ፋየሉን ይመልሳል።ከዚህ በሁዋላ ጉዳዩ ወደ ስዩም መሰፍን ይመራል። ስዩምም የዶ/ር ክንፈ መሆኑን ሲያዉቅ በቀይ ብእር **ይፈቀድላቸዉ** በሎ መርቶ ይመልሰዉና እቃዉ ያለ ምንም ጥያቄ ወደ አገር ወሰጥ እንዲገባ ሆነ። የእቃዉ ዝርዝር ዲፕሎማቲክ ኢሚዩኒት ስለነበረዉ ምን እንደሆነ ልናዉቀዉ አልቻልንም። እንግዲህ እዩልኝ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የሁለት አገር ዜጋ መሆን ህገ ወጥ ነዉ።ክንፈ ግን ይችላል። በሌላ ግዜ ደግሞ የኢትዮጵያን ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይዞና ኢትዮጵያን ወክሎ ከሄደበት አገር ሁሉ ለኢትዮጵያዊያን ብቻ በተሰጠ መብት መኪናዎችን እያመጣ ከቀረጥ ነፃ በማስገባት አዲስ አበባ ዉስጥ ይሸጣቸዋል። ከቀረጥ ነፃ ለማሰገባት የራሱ ህግና ደንብ ያለዉ ቢሆንም ያ ህግ ግን ለክንፈና ለመሰል ህወሃቶች አይሰራም ነበር።

ይህ ሰዉ የሚመራዉ ድርጅት ሶስት መልክ አለዉ።የመጀመሪያዉ ልክ እንደ ወጭ አገር ኢምባሲዎች እቃዎችን ከቀረጥ ነፃ የማስገባት መብት ያለዉ ድርጅት፤ ሁለተኛዉ ምንም እንኳ በዉጭ ጉዳይ ስር የሚተዳደር ቢሆንም እንደ ገለልተኛ የኢትዮጵያ መንግስት አማካሪ በመሆን ሁኔታዎች ሁሉ እየተሟሉለት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች በብዙ ሚልዮን የሚቆጠር ዶላር በእርዳታ መሰብሰብ፤ ሶስተኛዉ የዉጭ ጉዳይ ሰራተኞችን አሰለጥናለሁ በማለት ከፍተኛ በጀት እንዲመደብለት መጠየቅ። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ግሩም የሆነ ሬስቶራንት ከቢሮዉ ሰር ያለዉ ሲሆን ከሬሰቶራንቱ ጎን ደግሞ አንድ መፅሃፍት መሸጫ መደብር አለ።በዚህ መደብር ውስጥ የክንፈ መፃፎች እየተሸጡ የሚገኘዉ ገቢ ደግሞ ቀጥታ ለክንፈ ነዉ። እንግዲህ በስንት መልኩ የአገሪቷን ገንዘብ እንደሚዘርፉ ልብ በሉልኝ። ለዚህ ነዉ አንዳንድ በስብሰባዉ ላይ የነበሩ የትግራይ ልጆች ተናደዉ ክንፈን በድፍረት ለመናገር የበቁት። እኛ ግን ለትግራይ ለጆች የምንመክረዉ ነገር ቢኖር መናደድ ያለባቸሁ ክንፈን በመሰሉ ግለሰቦች ላይ ሳይሆን ለእነዚህ አይነቶቹ ሰግብግብ ባለሰልጣናት ገደብ ባላበጀ በዘረኛዉና በነፍስ ገዳዩ ህ.ወ.ሃ.ት. በዘረጋዉ ደካማ ሰርዐት ላይ ነዉ። ህወሃትን እየደገፉ ክንፈን መቃወም ቁም ነገር ያለዉ ነገር ሊሆን አይችልም።

በመጨረሻም ያ ከአራት ጫማ በላይ የማይረዝመዉ ዶ/ር ክንፈ አብርሃ ዋናተኞች የሚያደርጉትን ዓይነት ትልቅ መነፅር ከዐይኑ እንደ ሰካ በምድረ ኢትዮጵያ በሰላም ሙቶ ተቀብሯል። የኢትዮጵያ ቴሌቪዠንም ኢትዮጵያ "ድንቅ ልጇን" አጣች ብሎ እንዳረዳን እርማችንን አዉጥተናል።ክንፈ ቢሞትም ሌላዉ የህ.ዉ.ሃ.ት ከፍተኛ ካድሬዉ ስብሃት ነጋ እየተጎተተ ሂዶ በቦታዉ ተተክቷል። ታዲያ ምን አለበት ከኦሮሞ ከአማራ ከደቡብ ወይም ከሌላ ብሄሮች ዉስጥ ችሎታ ያለዉ ሰዉ ተፈልጎ ሲታጣ "ሊቁ" ስብሃት ነጋ ቢሾም?!የትግራይ ነፃ አዉጭዎች የታገሉትስ ለዚህ አይደል ? ሊቃነ ዘራፊዎችን ለማዘመን ?!!አይ አገሬ ኢትዮጵያ ለምን ይሆን እንዲህ የቀን ዠቦች የተቀራመቱሽ?

### *ነፃ ተጓዦች*

የወያኔዎችን ብልግናና ይሉኝታ ቢስነት የሚገልፁ እጅግ አፄያፊ ክስተቶችን በአገዛዝ ዘመናቸዉ ተመልክተን አግዚኦ ብለን አብቅተናል። በዉጭ ጉዳይ በኩል የሚፈፅሙትን የስልጣን ብልግና ስናጫዉታችሁ መገረም ወይም ደግሞ ያለመገረም መብታችሁ የተጠበቀ ነዉ።

አንድ ቀን የወያኔዎች ወንድም ወይም ደግሞ የአንዱ ልጅ በሆንኩ ብየ ተመኘሁ።አሁን ቁጭ ብየ ሳሰበዉ ግን ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዱ ስላልሆንኩ እግዚአብሄርን አመሰግነዋለሁ። በኩፉዎች መንገድ ያልሄደ እርሱ ምስጉን ነዉ የሚል የመፀሃፉ ቃል ትዝ ስላለኝ። እነሆ የነፃ ተጓዦች ነገር... የእነርሱን ዝምድና ያስመኘኝ አሳፋሪ ነገር፤

የወያኔ ባለስልጣናት ለአንዳች ጉዳይ ወደ ውጭ በተጓዙ ቁጥር ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እየተዘጋጀላቸዉ አጅበዉ የሚጓዙትን ዘመድ አዝማዶች ቁጥር እግዜር ብቻ ነዉ የሚያዉቀዉ። ልጆች ወንድሞች የወንድም ልጆች የሚስቶቻቸዉ ዘመዶች እረ ሰንቱን ቆጥረን እንችለዋለን ዘመዶቹ? እነሱ ለሽርሽር በሄዱ ቁጥር የዲፕሎማቲክ ቪዛ ሰራተኞች አስቸኳይ እየተባሉ መዋከባቸዉ ግን ያሳዝናል። የግብር ከፋዩ ገንዘብ በእነዝህ ከንቱ ባለስልጣናትና ዘመዶቻቸዉ አማካኝነት እንዲሁ በመባከኑ እጅግ አዝነን ወጥቶልናል። ይህ ሁሉ ወጭ የመ/ቤቱ የሂሳብ አሰራር በሚፈቅደዉ መሰረት የተወሰነ የወጪ ርእስ ስለሌለዉ በሺዎች የሚቆጠር ዶላር ልዩ ልዩ ወጭ ተብሎ ይመዘገባል።በቃ ማንም አይጠይቀም።

ይህ ሁኔታ የሚፈፀመዉ በዉጭ ጉዳይ ባሉ ባለስልጣናት ብቻ ሳየሆን በራሱ በመለስ ዜናዊ እና በዙሪያዉ በተኮለኮሉ አማካሪ ተብየዎችም ጭምር ነዉ።የአዜብ መስፍን፡ የንዋይ ገ/አብ፡የቁጡዉና ትእቢተኛዉ ሙሉጌታ ልጆችና ዘመዶችም ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እየያዙ በመንግስት ወጭ ሽርሽር እንደሚሄዱ በውጭ ገዳይ በዲፕሎማቲክ ቪዛ ዋና ክፍል ይሰራ የነበረ ወዳጄ አጫዉቶኛል። ኢትዮጵያዊያን በቀን አንድ ዳቦ አግኝተዉ መብላት አቀቷቸዉ በራብ አለጋ እየተገረፉ ባሉበት ሁኔታ እነዚህ ዋልጌ ባለስልጣናትና ዘመዶቻቸዉ እንዲህ ሲቀማጠሉ ስናይ እረ ለመሆኑ ይህች አገር የማን ነች ብለን እንድንጠይቅ ሆነናል።

### *በመጨረሻም*

በመጨረሻም ይህች አገር የሁላችን እየሆነች አየደለም።በዚህ 18 ዓመት ዉስጥ አገሪቷን የተቆጣጠሯት ጥቂት ማፊያና ዘረኛ ሃይሎች የሰዉ ልጅ ያደርገዋል ተብሎ የማይገመተዉን በደል በኢትዮጵያዊያኑና በኢትዮጵያችን ላይ ፈፅመዋል። ለብዙ ዲፕሎማቶችና ኢትዮጵያዊያን ሞት እንግልትና ስደት ምክንያት ሁነዋል። በእነዚህ ሰውንም እግዚአብሄርን በማይፈሩ ጨካኝ ቡድኖች ዘመን ኢትዮጵያችን በሁሉም መስክ ተዋርዳለች። ዲፕሎማቶቹ በውጭ አገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጋር እየተገናኙ የአገራቸዉን ገፅታ እንዳያድሱ በካድሬዎቹ አጥር ተከልክለዋል። በዚህም ምክንያት ብዙ የውጭ ምንዛሪ ወጥቶባቸዉ የተላኩበትን አገር እየተው መሰደድ ግድ ሁኖባቸዋል።

የዉጭ ጉዳይ መ/ቤት ሰራተኛዉ በካድሬዎች ነፃነቱን ተገፍፎ የሚያመነዉን ሳይሆን የማያምነዉን እየፈፀመ በባርነት ውስጥ የሚኖር ነዉ።ስዩምና አጫፋሪዎቹ ሰራተኛዉ ነፃ ሁኖ ለአገሩ የሚበጅ ነገር እናዳያስብና እንዳያደርግ ወዶና መርጦ ባልሆነዉ ዘሩ እንዲደራጅና በዘሩ ብቻ እንዲተሳሰር በማድረግ እንደ አንድ አገር ዜጋ የጋራ አቋም እንዳይኖረዉ በርትተዉ ይሰራሉ።ለዚያች ድሃ አገር ሊጠቅም የሚችል በጎ ተግባር ከመስራት ይልቅ አንዱ አንዱን ፈርቶና ጠርጥሮ እዉነተኛ ፍላጎቱን ደብቆ በከንቱ ስሜት እንዲባክን ያደርጉታል። ከዚህ ዓይነቱ ሰሜት ወጥቶና ደፍሮ አንድ ሁለት አስተያየት የሰጠ ከተገኘም ያለምንም ቅደመ ሁኔታ እንዲባረር ይደረጋል።

በዚህም ኦሮሞዉ አነግ አማራዉ ነፍጠኛ ሁነዉ እርስ በርሳቸዉ ለአንድ በጎ ዓላማ አንድ ላይ እንዳይቆሙ ለማድረግ የእነዚህን ትላልቅ ብሄር አባላት ልጆች አንድነት ይሸረሽራሉ። አንዱ ለአንዱ ስጋት እንደሆነ አድርገዉ ለማሳየት ይጥራሉ። በተወሰነ ደረጃ የተሳካላቸዉ የሚመስልበት ሁኔታ አለ። ኦነግ ስልጣን ከሚይዝ ህዉሃት እዚያዉ እየበላኝ ቢቀመጥ ይሻላል ይላል አማራዉ በሌላ በኩል ደግሞ ኦሮሞዉ ነፍጠኛ(አማራዉ) ስልጣን ላይ ከሚወጣ ህዉሃት እዚያዉ ቢቀመጥ እመርጣለሁ ይላል። ህዉሃት የሚመኘዉ የሄንኑ ነዉ፤ በዚህ መካከል ህዉሃት እድሜዉን እያራዘመ የኦሮሞዉንም የ አማራዉንም ስቃይ እያበዛ ያሻዉን እያደረገ ይኖራል።

ባጠቃላይ ባገሪቷ ጥቂቶች ብዙሃኑን ተጭነዉ ብዙሃኖቹ ደግሞ ጥቂቶቹን ተሸክመዉና አሳራቸዉ በዝቶ የሚኖሩባት አገር ነች። ጥቂቶች ታጋዮች ብቻ በልተዉና ጠጥተዉ ሆዳቸዉን ሞልተዉ ደስ በሎአቸዉ የሚኖሩባት ብዙሃኑ ግን የሚራቡባትና የሚሰደዱባት አገር ነች ኢትዮጵያ።እነዚህ ታጋይ ተብየዎች ያ የማይሞላ ከርሳቸዉን ለመሙላት ሲሉ ቢሰርቁ ቢያሳድዱ ቢያስሩ እና ቢገድሉ የሚከለክላቸዉ ምድራዊ ህግ ስለሌለ በአንዲት ጀንበር አሉ የሚባሉ ሃብታሞች ሁነዉ እናያቸዋለን።

በዚህም መሰረት የህወሃት መሪ መለስ ዜናዊ 1.2 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሃብት ባለቤት በመሆን ከዓለም መሪዎች መካከል 11ኛው ሃብታም መሆኑን በተለያዩ ሚዲያዎች ወጥቶ አይተናል።እንደምን ሁኖ እንዲህ ከሃብታሞቹ አገራት በልጦ ሃብታም ሊሆን እንደቻለ መጠየቅ ግድ ይሆንብናል። ወ/ሮ አዜብም የመለስ ዜናዊ ሚስት እናንተ እኮ ድሆች ናችሁ ተብላ ለቀረበላት ጥያቄ መልስ ስተሰጥ በመገረም ማን? እኛ? እረ የማታውቁቱን አታውሩ! እኔ ድሃ አይደለሁም መለስም ድሃ አይደለም ብላ መልስ መስጠቷን አይተን ተደምመናል።

**ክፍል 5 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀርባል**

## ኢትዮጵያዊያን በሎንዶን ከፍተኛ የሆነ የተቃዉሞ ሰልፍ አደረጉ

በሎንዶን የሚገኙ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን የዘረኛና አምባገነኑን መለስ ዜናዊን ወደ እንግሊዝ መምጣት ምክንያት በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የተቃዉሞ ሰልፍ አደረጉ። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲሕ የውጭ ሓገራት መንግስታትን ሳይቀር የፈለግሑትን አደርጋለሑ ምንስ ታመጣላችሑ የሚልና ፍጹም የሖነ አምባገነንነቱንና ጨካኝነቱን በግልጽ የሚያሳዩ ተግባራትን እያከናወነ ያለው ዘረኛው መለስ ወደለንደን የመጣበት ዋነኛው ምክንያት ቀደም ብሎ በኮፐን ሓገኑ ስብሰባ እንዳሰበው ያልተሳካለትን ነገር ግን ጥቂትም ፍርፋሪ ቢሖን ወደካዝናየ ማስገባት አለብኝ በሚል ቅዠት ቆርጦ የተነሳበትን የገንዘብ ማጋበስ ሕልም ተግባራዊ ለማድረግ እንደሖነ ታውቋል።

በትናንትናው እለት በተካሔደው በዚሑ የለንደኑ የኢትዮጵያዊያን የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የተገኙ ኢትዮጵያዊያን ባሰሙት ጩኸት የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚንስትር ጎርደን ብራዉን እንደኦሳማ ቢንላደን ካለ አሸባሪ ጋር የአለማችንን የሽብርተኝነት መዋጋት ዘመቻ ለማሳካት አጋር ማድረጋቸው አሳዛኝ እንደሆነ ገልጸዋል። ሰልፈኞቹ ባሰሙት ጩኸት በከፍተኛ ሑኔታ የሰው ልጆችን መብት እየጣሰ እንደሆነ ከሚታወቀውና ያለምንም የሕዝብ ይሑንታና ፈቃድ በስልጣን ወምበር ላይ ከተፎጠጠው መለስ ዜናዊ ጋር ቁጪ ብሎ የአለማቹን ሌላው ቹግር ስለሖነው የአየር ንብረት መዛባት ችግር መፍትሔ ለማፈላለግ መነጋገርም በጣም የሚያሳፍር ነው ብለዋል። በመቀጠልም ሰልፈኞቹ ኢትዮጵያዊያን ባሑኑ ወቅት በጨፍጫፊው መለስ ዜናዊ በተቀነባበረ ሽብር ስቃይ እያዩና ለእልቂትም እየተዳረጉ እንደሖነ እነጎርድን ብራውን ሊገነዘቡ ይገባል ካሉ በሑዋላ እንግሊዝም ሖነች ሌሎች ሓገራት የመለስ ዜናዊን የአገዛዝ እድሜ ለማራዘም የሚያደርጉትን ድጋፍ ሊያቆሙ እንደሚገባ አስጠንቅቀዋል።

ኢትዮጵያዊያኑ በዚሑ የተቃውሞ ሰልፍ የወይዘሪት ብርቱካን ሚዴቅሳን ፎቶግራፎችና በርካታ መፈክሮቹን በመያዝ ጩኸታቸዉን ሲያሰሙ የዋሉ ሲሆን ከነኚሕም ውስጥ ብርቱካን ሚዴቅሳ ባስቸኳይ ከእስር ትፈታ፤ ገዳዮችን መሸከም በቃን፤ እኝግሊዝ ለጨቋኝና አምባገነን አገዛዝ የምታደርገውን እገዛ ባስቸኳይ ታቁም፤ መለስ ዜናዊ ለፈጸመው የዘር ጭፍጨፋ ከአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ፊት ሊቆም ይገባል፤ መለስ ደም መጣጭ አረመኔ ነው፤ በኢትዮጵያ ምንም ነጻ ምርጫ የለም፤ የሚታሰብም አይደለምና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል፡፡

ከዚሑ ዜና ጋር በተያያዘ አምባገነኑ መለስ ወደለንደን የመጣበት ጉዳይ የመሳካት እድሉ አጠራጣሪ እንደሖነ ከተባበሩት መንግስታት ጽ/ቤት የወጣ መረጃ ገለጸ። የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ጉዳይ ክፍል ባወጣው በዚሑ መረጃ እስከ 2011 ባለው ጊዜ ውጽጥ በኮፐን ሓገን ተደርጎ የነበረው ስምምነት ገቢራዊ ይሖናል የሚል ተስፋ እንደሌለው በዚሁ መግለጫው ላይ አስታውቋል።

## በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች . . . ከገጽ 1 የዞረ

በመረዳታቸው የሚይዙትና የሚጨብጡትን አጥተው ፍርሃትና ጭንቀት የወለዳቸውን ስድብ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ ያዘሉ መግለጫዎች እየሰጡ ነው ፤ የህዝቡን ነፃ ተሳትፎና የተቃዋሚ ድርጅቶችን ነፃ እንቅስቃሴዎች የሚገድቡ የተለያዩ አዋጆችም ሲደነግጉ በዓይናችን እያየን ነው ብሏል።

በሌላም በኩል አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ራሱ ዕጩ ተወዳዳሪ ሆኖ እያለ ነገር ግን ራሱ አወጣሁት ካለው ከሕገ መንግስቱ፣ ከምርጫ ቦርዱና ከምርጫ ስነ ምግባሩ ሕግ በላይ በመሆንና የአምባገነንነት ጡንቻ ስልጣኑን መከታ በማድረግ በሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ላይ ተደጋጋሚ የስነ ልቦና ጦርነት ሲያውጅ ሰምተናል ስል አትቷል። መግለጫው በመቀጠል ይህ በአፀያፊ ስድብና አስደንጋጭ ቃላት እየታጀበ ነጋ ጠባ የሚጎሰመው የጦርነት ነጋሪትና እሱን ተከትሎ እየተወሰዱ ያሉት ሕገ ወጥ እርምጃዎች አላማቸው በአንድ በኩል የምርጫውን ሂደት በማደፍረስና አቅጣጫውን በመቀየር የህዝቡን ድምፅ በአቋራጭ ለመንጠቅ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች ማመቻቸት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቡ በሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበትና ለማደናገር ብሎም ከሁሉም በላይ በሀገሪቱ ትርጉም ያለውና በአስተማማኝ ህዝባዊ መሰረት ላይ የተገነባ ተቀናቃኝ የፓለቲካ ድርጅት እንዳይፈጠር የህዝቡን ተስፋ አጨልሞ አንገቱን ለማስደፋት መሆኑን ተገንዝበናል ሲል ገልጿል።

የትግራይ ተወላጆች ስብስብ የጋራ አቋምና መግለጫ 80 ሚሊዮን ህዝብ የሚመለከት የምርጫ ጉዳይ በአንድ አምባገነን ፈላጭ ቆራጭ መሪ እጅ ወድቆ ከሕግ በላይ በመሆን ራሳቸው ዕጩ ተመራጭ፣ ራሳቸው አሳሪ፣ ራሳቸው ፍርድ ሰጪ በመሆን ሀገሪትዋን እንደ ፈለጉ ሲነዱዋትና ሲያተራምሱዋት ማየታችን እጅጉን አሳዝኖናል፤ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ኮሚኒስታዊ ስርዓት ስር የተዋቀሩ የፍትሕና የመንግስት አካላትም የዳር ተመልካችና የወር ደመወዝ ጠባቂዎች እንጂ ሕገ መንግስቱንና የህዝቡን ሰብአዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ዜግነታዊ መብቶች ሲጠብቁና ሲያስከብሩ አይታዩም ብሏል። እነዚህ ተቋማት ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ ታማኝ የሆነ ሰው ብቻ የሚንከባከቡ እንጂ ሕግን አክብረው በሰላም ለሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሕግ ከለላና የሕግ ዋስትና ሲሰጡ አላየንም ካለ በኋላ፣ ተቋማቱ ለኢሕአዴግ መንግስታዊ ልባስ ለመስጠት የተፈጠሩ እንጂ ምርጫው ፍትሓዊ፣ ሚዛናዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ተአማኒ እንዲሆን የመቆጣጠር፣ የመፈፀምና የማስፈፀም ዓቅሙም ብቃቱም ፍላጎቱም እምነቱም የሌላቸው፣ በአንድ አምባ ገነን መሪ የሚሽከረከሩ፣ በአንድ ሰው ሳምባ የሚተነፍሱ፣ ጥርሰ አልባና ህይወት የሌላቸው ጉዑዛን ሆነው ማየታችን እጅጉን አሳዝኖናል ብሏል።

በመጨረሻም መግለጫው የተላለፈው የስም ማጥፋት ዘመቻ መሰረት የሌለው፣ በአልቧልታና በቂም በቀል ላይ የተመሰረተ፣ ለመጪው ትውልድም መጥፎ የታሪክ ጠባሳ ጥሎ የሚያልፍ እርምጃ በመሆኑ በአስቸኳይ እንዲታረም (**ወደ ላይ ይቀጥላል**)

## እጩ ተወዳዳሪዎች ራሳቸውን ከምርጫ ማግለል ጀመሩ

በትናንትናው እለት የአሜሪካው ሬዲዮ የአማርኛ ዝግጂት ክፍል ባቀረበው ፕሮግራሙ ከመቶ በላይ የሚሆኑ የመኢአድ እጩ ተወዳዳሪዎች ከገዢው ፓርቲ በደረሰባቸው የተለያዩ ተጸእኖዎች ምክንያት ራሳቸውን ከምርጫ ማግለላቸውን መኢአድ ያስታወቀ ሲሆን ለምርጫ ተመዘገቡ ከተባሉ ፓርቲዎች ደግም አስራ ሰባት የሚሆኑት በምርጫው እንደማይሳተፉ ተገልጿል። ከዚሁ ዘገባ ጋር በተያያዘ በሃገሪቱ እየታተም የሚሰራጨው ሪፖርተር ጋዜጣ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድን አጣቅሶ የየፓርቲዎቹን የፓርላማ ምክርቤትና የክልል ተወዳዳሪ እጩዎች ቁጥር በእትሙ ያወጣ ቢሆንም ከብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ተሰጠ የተባለው የተወዳዳሪዎች ቁጥር ተወዳዳሪ ፓርቲዎቹ አስመዝግበናል ካሉት ተወዳዳሪዎች ቁጥር ጋር የማይጣጣምና የተለያየም መሆኑ ታውቋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም የመራጮች ምዝገባ ተጠናቆ የተለያዩ ተቋማት ተማሪዎችንና የጦር ሰራዊቱን ሳይጨምር ከ29 ሚሊዮን በላይ መራጮች ካርዳቸውን መውሰዳቸውንም ጨምሮ ገልጿል።

የይስሙላ ምርጫን የእውነት ምርጫ ለማስመሰል የትያትር ትወናዉን ለማሳየት እየተንደፋደፈ ያለው የወያኔው አምባገነን አገዛዝ ይህ ድርጊቱ በሃገር ውስጥ ባሉት ኢትዮጵያዊያን በግልጽ ከመታወቅ አልፎ የወያኔው ግፈኛ አገዛዝ እየተጫወተ ያለው ድራማ ብዥታ ፈጥሮባቸው ሲደናበሩ የነበሩት ምእራባዊያን መንግስታት ሳይቀር ዘግይተው እየተገነዘቡት መምጣታቸው ከእለት ወደ እለት እየታየ በምምጣት ላይ ያለ ለመሆኑ በርካቶች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው።

በኢትዮጵያ የሚታተመውን የሪፖርተር ዘገባና የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያሰሙትን የተቃረነ እውነታ አስመልክቶ አዲስ አበባ የሚገኘው የግንቦት ሰባት ዘጋቢ አስተያየት እንዲሰጡት የጠየቃቸው ስማቸው እንዳይገለጽ ያሳሰቡ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በሰጡት አስተያየት አሁን እየሰማነው ያለነው ነገር በሙሉ ቀደም ብሎ የይስሙላ ምርጫው ሽር ጉድ ሲባልለት ጀምሮ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግምት ውስጥ የነበረ እንደሆነ ገልጸው የበለጠም ወደምርጫው በተቃረብን ቁጥር ገና ሌሎች አስገራሚ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ያላቸውን ግምት ጸጥተዋል። አስተያየት ሰጪው በመቀጠልም የምረጡኝ ዘመቻው እንኳን ገና መስመር ባልያዘበት ሁኔታ እንዲሁም የመራጩ ህዝብ ቁጥር በትክክል ታውቋል ተብሎ የውሸት ፕሮፓጋንዳ በሚነዛበት ሂደት እጩ ተወዳዳሪዎች ራሳቸውን ከምርጫ እያገለሉ መምጣታቸው እንዲሁም በርካታ ፓርቲዎችም በውድድሩ እንደማይሳተፉ ማረጋገጣቸው የምርጫውን የይስሙላነት የሚያረጋግጥ ነው ካሉ በኋላ ድሮውንም ቢሆን የወያኔን ማንነት እያወቁ ወያኔ በምርጫ ስልጣን ይለቃል በሚል ተስፋ ለውድድር መገባቱ ትርጉም የሌለው የጉንጭ አልፋ ድርጊትነቱን ያሳያል ብለዋል።

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ በተደጋጋሚ እንዳሳወቀውና ለኢትዮጵያዊያንም ጥሪዉን እንዳቀረበው የወያኔው ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ በምንም አይነት ስልጣኑን በምርጫ እንደማይለቅ ይልቁንም ለዚህ መድሃኒቱ ሁለገብ የሆነ ትግል እንደሆነ ሲያሳውቅ መቆየቱ ይታወቃል።

በተያያዘ ዜናም ግንቦት7 የአውሮፓ ህብረት የዘንድሮውን ዬይስሙላው ምርጫ ለመታዘብ መወሰኑን በመቃወም መግለጫ አውጥቷል። ንቅናቄው በመግለጫው የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮን አፍናለሁ ብሎ በአደባባይ የተናገረና እጩ ተወዳዳሪዎችንም ከምርጫው በሁዋላ አስራለሁ ብሎ የዘተ አምባገነን፣ ትክክለኛና ፍትሀዊ ምርጫ ያደርጋል ብሎ መጠበቅ ራስን ማታለል ነው ብሎአል። የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን ውሳኔውን እንደገና እንዲመረምር የጠየቀው ግንቦት7፣ ለዲሞክራሲና ለፍትህ ሲሉ ከኢትዮጵያውያን ጋር እኩል መስዋትነት በመክፈል ላይ ላሉት ሚስ አና ጎሜዝ ያለውን ከፍተኛ አድናቆት ገልጿል።

የፕሮግራሙም አዘጋጆች የዜና ስርዓት መብታቸውን ጠብቀው የሚያቀርቡት ዜናም ሆነ ዝግጅት የህዝቡን ብሶትና የሀገር ጉዳይ ማእከል ያደረገ እንዲሆን አቀራረባቸውም ድፍረት፣ ነፃነት፣ ግልፅነት፣ ሚዛናዊነትና ሞያዊ ብቃት የተላበሰ እንዲሆን ከአክብሮት ጋር አደራ እንላለን ብሏል።

የትግራይ ተወላጆቹ የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱን ለማስከበርና እንዲሁም የስልጣኑ ባለቤት ለመሆን በምርጫው ዙሪያ በሚያደርገው የነቃ ተሳትፎና ሰላማዊ እንቅስቃሴ ሁሉ እየተከታተሉ እስከመጨረሻ ከጎኑ በመቆም ዜግነታዊ ድርሻቸውን ለመወጣት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸው አምባገነኖች ዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም በሰለጠነበት ወቅት ስለሀገራችን ጉዳይ እንዳንሰማ ጆሮኣችንን፣ እንዳናይ ዓይናችንን፣ እንዳንናገር አፋችንን ዘግተውና አፍነው በመያዝ እውነትን መሸፈንና ዘላለም ህዝብን ማታለል እንደማይችሉ ሊያውቁት ይገባል በማለት መግለጫቸውን አጠናቀዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ውድ አንባቢዎቻችን
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661